Remove Watermark Wondershare PDFelement

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ገንዘብ ቢሮ

AMHARA NA
BUREAU OF FINANCE

ቁጥር አብክመ/ገ/ፈ/128

ቀን 30/10/2014

ለ 31 ቢሮ/ኮሚሽን/ኤጀንሲ/ባለስልጣን/ጽ/ቤት
ባህር ዳር፤

ለ 19 ዞን/ሜትሮፖሊታንት/ከተማ/ ገንዘብ መምሪያ
_____፤

ጉዳዩ፡- <u>የግንባታ ስራዎች ዋጋ ንረት ማስተካከያን ይመለከታል</u>፤

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰኔ 10 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው 6ኛ ዙር አንደኛ ዓመት የሰራ ዘመን 5ኛ መደበኛ ስብሰባ በዋጋ ንረት ምክንያት በግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ እያጋጠመ ያለውን ችግር ለመፍታት ከተለያዩ ቢሮዎች የተውጣጣ ቴክኒካል ኮሚቴ ባቀረበው የዋጋ ንረት ጥናትና ማስተካከያ ምክረ ሀሳብ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፉን በቁጥር አብክመ 11/1153/መ-ከ-1 በቀን 20/10/2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቋል።

በመሆኑም በክልላችን በተለያዩ ምክንያቶች ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ የግንባታዎችን የዋጋ ንረት ተጽዕኖ በጥናት ላይ ተመስርቶ የመፍትሄ ሃሳብ ለመስጠት የ2012 በጀት ዓመትን መነሻ በማድረግ እንደየ ፕሮጀክቶች የስራ ዓይነት በመከፋፈል ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ የዋጋ ንረት ማሻሻያ ውሳኔ አሳልፏል።

ስለሆነም በተወሰነው ውሳኔ መሰረት የግንባታ ፕሮጀክት ያላችሁ ተቋማት በአግባቡ የዋጋ ንረት ማስተካከያውን በጥንቃቄ ተግባራዊ እንድታደርጉ እያሳሰብን ለአፈጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ 06 ገጽ የአፈጻጸም ስርዓት አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እያሳወቅን፤የክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤትና የየመ/ቤቱ የውስጥ ኦዲተሮች የዋጋ ንረት ማስተካከያው በተላለፈው የአሰራር ስርዓት መሰረት መፈፀሙን እንድትከታተሉ እያስታወቅን የዞን ገንዘብ መምሪያዎች ይህን የዋጋ ንረት ማስተካከያ በስራችሁ ለሚገኙ የከተማ አስተዳደሮች፤ወረዳዎች እና ለክልል ተጠሪ ተቋማት እንድታሳውቁ እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

ያሳሁን መሐሪ አንተነህ(ዶ/ር)ኒ
ቢሮ ኃላፊ

<u>ግልባጭ</u>፤

- ለርዕሰ መስተዳድርና ክልል መስተዳድር ጽ/ቤት
- ለዋና ኦዲተር መ/ቤት
  <u>ባህር ዳር</u>፤
- ለመንግስት ግዥና ንብረት አስ/ኦ/ክ/ጥ/መ/ት/ ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት
- ለኢንፎርሜሽን ኮሙ/ቴክ/ዳይሬክቶሬት
  <u>ገንዘብ ቢሮ</u>

ስልክ ፋክስ ኢ.ሜል ድህረ ገጽ ፖስታ ሣ.ቁ
TEL 058 220 0794 Fax 0582 265398 Email bofec1988@gmail.com Website WWW.amharabofec.goV.et P.o.Box 217/621

Remove Watermark Wondershare PDFelement

በግንባታ ግብዓቶች ላይ በተፈጠረ የገበያ ዋጋ ጭማሪ ምክንያት የተደረገ የዋጋ ንረት ማሻሻያ የአፈጻጸም ስርዓት

1. መግቢያ

በሀገራችን በሚከናወኑ የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ተገማች ባልሆኑ ምክንያቶች የግንባታ ግብዓቶች ዋጋ ጭማሪ በማጋጠሙ የስራ ተቋራጭ (ድርጅቶች) ከልዩ ልዩ የክልላችን ተቋማት ጋር የግንባታ ዉል ቢይዙም በዋጋ ንረት ምክንያት ሊጠናቀቁ አልቻሉም፡፡

ስለሆነም ክልላዊና ሀገራዊ በሆነ መንገድ የተከሰተዉን ያልተረጋጋና ተገማች ያልሆነ የግንባታዎችን ግብዓት የዋጋ ንረት ያስከተለዉን ችግር ለመፍታት የክልላችን መንግስት ለስራ ተቋራጮቹ የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ በወሰነዉ ዉሳኔ መሰረት የተለያዩ ጥናቶች ሲካሄዱ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም በዋጋ ንረት ማስተካከያ ቀመር መነሻ በማድረግ በቀሪ ስራዎች ላይ የዋጋ ማስተካከያ ሊደረግላቸዉ የሚገባቸዉን ስራዎች በመለየት እንዲሁም በዋናነት የክልሉ መንግስት ካለዉ የበጀት ዕጥረት አንጻር ስራ ተቋራጮችን ደግፎ ፕሮጀክቶችን ለማስጨረስ ሲባል ባልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወደፊት እየተሰሩ በሚመጡ ቀሪ ስራዎች ላይ ብቻ የዋጋ ማሻሻያ እንዲደረግ ወስኗል፡፡

2. የተፈጻሚነት ወሰን፤

ይህ የዋጋ ንረት ማሻሻያ ተፈፃሚ የሚሆነው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚደገፉ የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ይሆናል፡፡

3. የዋጋ ንረት ማካካሻ የሚደረግበት ሁኔታ፤

የዋጋ ንረት ማካካሻ የሚተገበረው ላልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ሆኖ ከመጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በኋላ ለተሰሩና ለሚሰሩ ቀሪ ስራዎች ብቻ ይሆናል፡፡ ስለሆነም እስከ መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰራ ስራ በክፍያ ሰርተፊኬት የተረጋገጠም ይሁን ያልተረጋገጠ ስራ የዋጋ ንረት ማሻሻያ አይመለከተውም፡፡

በመሆኑም ከመጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በኋላ ለተሰራ ስራ በሚቀርበዉ ክፍያ ላይ በዋጋ ንረት ማስተካከያዉ የማባዣ ፐርሰንት በማባዛት ጭማሪዉ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

Remove Watermark Wondershare PDFelement

4. <u>ከግንባታ ዉል አንጻር፡</u>

በግንባታዎች ላይ የተከሰተዉ የዋጋ ንረት አሁን ካለንበት 2014 በጀት ዓመት በፊት ባሉት ዓመታት በተለያዩ መረጃዎች በተረጋገጠዉ መሰረት የዋጋ ንረቱ በየዓመቱ የተለያየ በመሆኑ በዚህ ምክንያት ቀደም ሲል ለረጅም ዓመታት ተጀምረዉ እስካሁን ያልተጠናቀቁትን በሙሉ ታሳቢ በማድረግ ሁሉም ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ዉለታ ከተፈጸመባቸዉ ጊዜ አንጻር በ3 ተከፍሎ እንዲታይ ተደርጓል፡፡

እነዚህም፡-

1. ከሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም እና በፊት ዉል የተወሰደባቸው ፕሮጀክቶች፣
2. ከሀምሌ1 ቀን 2012 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ዉል የተያዙ ፕሮጀክቶች፣
3. ከሀምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ዉል የተያዙ ፕሮጀክቶች በሚል የተለዩ ሲሆን፡-

እነዚህ ፕሮጀክቶች እንደዉል ጊዜያቸዉ ተጨባጭ ሁኔታ የዋጋ ንረት ማሻሻያዉ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡

5. <u>የዋጋ ንረት ማስተካከያ የሚደረግባቸው የፕሮጀክት አይነቶች /Project Type/ ፡</u>

የግንባታ ዋጋ ንረት በሁሉም የፕሮጀክት አይነቶች የግንባታ ማቴሪያል ላይ ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም እንደፕሮጀክቱ ተጨባጭ ሁኔታ እና እንደሚጠቀመዉ ግብዓት ሁሉንም የፕሮጀክት አይነቶች ተመሳሳይ የዋጋ ማካካሻ ቀመር ከመስራት ይልቅ እንደፕሮጀክቶቹ ተጨባጭ ሁኔታ ለየራሳቸዉ የዋጋ ማካካሻ ቀመር መኖር እንደሚገባዉ ስለታመነበት ፕሮጀክቶችን እንደባህርያቸዉ የመለየት ስራ ተሰርቶ ለእያንዳንዳቸዉም የዋጋ ማስተካከያ ማባዣ ተጠንቶላቸዋል፡፡

በዚህም መሰረት የተለዩት ፕሮጀክት አይነቶች <u>/Project Types/</u> ፡-

1. የህንጻ ግንባታዎች /Building works/
2. የድልድይ ግንባታዎች /Bridge works/
3. የመስኖ ግንባታዎች /Irrigation works/
4. የመጠጥ ዉሀ ፕሮጀክቶች /water Supply projects/ እና
5. የመሬት ስራ /Earth work/ ናቸዉ፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ ባለፕሮጀክት ተቋም ፕሮጀክቶችን ከላይ በተቀመጠዉ መሰረት መለየትና መፈጸም አለበት፡፡

Remove Watermark Wondershare PDFelement

6. **የዋጋ ንረት ማባዣ በፐርሰንት እና አተገባበር፡**

6.1. ከላይ በተገለጸዉ መሰረት ከመጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በኋላ ለተሰሩና ለሚሰሩ ቀሪ ስራዎች የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ በጥናት እንደተገኘዉና ክልሉ ካለዉ የበጀትና ሌሎች ተጨባጭ ችግሮች አንጻር የምንጠቀመዉ የማባዣ ቀመር እንደየ ፕሮጀክት አይነቱ በፐርሰንት ቀጥሎ በተቀመጠዉ ሰንጠረዥ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ተ.ቁ	የዋጋ ንረት ማስተካከያ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ ገደብ	የዋጋ ንረት ማስተካከያ ማባዣ ፐርሰንት እንደ ፕሮጀክት አይነት				
		ለህንጻ ግንባታ	ለመስኖ ግንባታ	ለድልድይ ግንባታ	ለመጠጥ ዉሀ ፕሮጀክቶች	ለመሬት ስራ
1	ከሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም እና በፊት ዉል የተፈጸሙ ፕሮጀክቶች	30.95%	26.64%	26.07%	26.76%	11.23%
2	ከሀምሌ 1 ቀን 2012 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓም ድረስ ዉል የተያዙ ፕሮጀክቶች	21.02%	15.74%	18.60%	15.28%	6.28%
3	ከሀምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓም ድረስ ዉል የተያዙ ፕሮጀክቶች	10.79%	11.02%	12.96%	10.75%	2.36%

6.2. ከመጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በኋላ የተሰራዉን ስራ በዋጋ ማስተካከያ ማባዣ ለማስላት በሚቀርበዉ የክፍያ ሰርተፊኬት መሰረት እስካሁን የተሰሩ ስራዎች በገንዘብ ተሰልቶ ከቀረበዉ ላይ ከዚህ በፊት እስከ መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ በክፍያ ሰርተፊኬት የተረጋገጠም ይሁን በክፍያ ያልተረጋገጠ የተሰራ ስራ ተሰልቶ የተገኘዉን ገንዘብ በመቀነስ ልዩነቱን በተፈቀደው ፐርሰንት እንደ የፕሮጀክት አይነቱ በማባዣ የዋጋ ማካካሻዉ የሚሰላ /የሚታሰብ/ ይሆናል፡፡

በዋጋ ንረቱ ማስተካከያ የተገኘ ገንዘብ እስካሁን ከተሰራዉ ስራ ጋር በመደመር ጥቅል ዉጤቱ ላይ በመነሳት አስፈላጊዉን የማቀናነስ ስራ በክፍያ ሰርተፊኬቱ አሰራር መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

Remove Watermark Wondershare PDFelement

ለምሳሌ፤-

በየዙሩ ለሚቀርብ የክፍያ ሰርተፍኬት ላይ የዋጋ ንረት ማካካሻ የክፍያ መጠን ለማግኘት= (ከመጋቢት 30/2014 ዓ.ም በኋላ በክፍያ ሰርተፊኬት ተረጋግጦ ከሚቀርበው የግንዘብ መጠን - እስከ መጋቢት 30/2014 ዓ.ም የተሰራ ስራ ወይም ስራው ተሰርቶ በክፍያ ሰርተፍኬት ያልቀረበ ስራ) x በዋጋ ንረት ማስተካከያ ቀመር፡፡

6.3. <u>ግንባታዉ ከሚጠበቅበት አካላዊ ቁመና አፈጻጸም /Physical Progress/</u>፤-

አብዛኛቹ የግንባታ ስራ ተቋራጮች በተሰጣቸው የዉል ጊዜ ግንባታዉን ማጠናቀቅ ወይም የተሻለ አፈጻጸም ማድረስ የሚገባቸዉ ቢሆንም አሁን ካለዉ የግንባታ ስራዎች አፈጻጸም አንጻር አብዛኛው ስራ ተቋራጭ የሚጠበቅባቸዉን ያክል በተሰጣቸው የዉሉ ጊዜ መሰረት እየፈጸሙ አለመሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ ሲባል ሁሉም ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች በውል ስምምነቱ መሰረት መድረስ የሚገባቸዉን አፈጻጸም መሰረት ሳያደርግ ከመጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በኋላ ለተሰሩና ለሚሰሩ ስራዎች በቀረበዉ ቀመር መሰረት የሚተገበር ይሆናል፡፡

7. <u>የተጨማሪ እና የለውጥ ስራ የዋጋ ንረት ማስተካከያ አተገባበር፡</u>

የዋጋ ንረቱ የሚተገበረዉ ከዉሉ አንጻር ለቀሪ ስራዎች ሲሆን በተጨማሪ ዉል የተያዘ ተጨማሪ እና የለውጥ ስራ በተቋሙና በስራ ተቋራጩ በኩል የዉል ስምምነት የተፈረመበት ከሆነ ብቻ የተጨማሪ እና የለውጥ ስራዎች ከመጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በኋላ ለተሰሩና ለሚሰሩ ስራዎች የተፈረመበትን የዉል ቀን መሰረት በማድረግ የዋጋ ማካካሻ እንደዉሉ ቀንና እንደየፕሮጀክት አይነቱ ከላይ ለዋና ዉል የዋጋ ንረት ማስተካከያ አንቀጽ 6 ንዕስ አንቀጽ 6.1 በተቀመጠው መጠን መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

8. <u>ከመሬት ስራ ጋር የተያያዘ የዋጋ ንረት ማሻሻያ አፈጻጸም በተመለከተ</u>

8.1. ለመሬት ስራ /Earth work/ የተቀመጠውን የዋጋ ንረት ማካካሻ አሰራር ቀመር በመጠቀም የሚሰራ ይሆናል፡፡

8.2. እስካሁን ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች የመሬት ስራ ያልተሰራላቸው ማለትም የህንፃ፤ የመስኖ፤የመጠጥ ውሃ እና የድልድይ ስራዎች ውስጥ ከመጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በኋላ የተሰራና ሊሰራ የሚችል ካለ ለሁሉም ፕሮጀክቶች በተቀመጠዉ የመሬት ስራ የዋጋ ንረት

Remove Watermark Wondershare PDFelement

ማካካሻ ተብሎ በሰንጠረዡ ላይ እንደየፕሮጀክቱ የተቀመጠዉን ፐርሰንት በመደመር በሚገኘዉ ዉጤት የዋጋ ንረት ማስተካከያዉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

8.3. የመሬት ስራ /Earth work/ ሲባል በዋናነት፤-

ሀ. ለህንጻ ስራ፡-የትሬንች/Trench Excavations/ እና የበልክ ቁፋሮ፣ የሙሊት ስራ፣ ለ. በድልድይ ስራ፡- የቆረጣና እና የሙሊት ስራ፣

ሐ. በመስኖ ስራ፡-የግድብ የቆረጣ ስራ እና ሙሊት ስራ፣ የካናል ቁፋሮና ሙሊት ስራ ሲሆኑ

መ. የዉሀ መስመር ለመዘርጋት የሚተገበር የቁፋሮና አፈር የመመለስ /የሙሊት/ ስራ ብዙ ጊዜ ከዝርጋታዉ ጋር በጥቅል ዉል የሚያዝበት ስለሆነ ለዚህ ስራ የመሬት ስራ የማባዣ ፐርሰንቱ የሚደመር አይሆንም፡፡

9. <u>የዋጋ ንረት ማስተካከያ አፈጻጸምና በበጀት ምንጭ፤</u>

9.1. የዋጋ ንረት ማስተካከያውን ተግባራዊ ማድረግ በመንግስትና በስራ ተቋራጩ እየደረሰ ያለውን ጫና ለመቀነስ እና ፕሮጀክቶችን አጠናቆ ለተፈለገው ዓላማ እንዲውሉ ለማድረግ ከዚህ በላይ አንቀጽ 6 ንዕስ አንቀጽ 6.1 በተገለጸው ሰንጠረዥ መሰረት የዋጋ ንረት ማስተካከያ አንዲደረግና ለዚህም ተግባር የሚያስፈልገው ተጨማሪ በጀት በቀሪ ስራው ላይ ታሳቢ እየተደረገ እንዲከፈል፤

9.2. ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች በራሳቸው በጀት የሚሰሯቸው ፕሮጀክቶች በጀት ያላቸው ከሆነና የዋጋ ማስተካከያውን ለማድረግ ፈቃደኛ ከሆኑ ለክልል ቢሮ ፕሮጀክቶች የተፈቀደውን የዋጋ ንረት ማስተካከያ ቀመሩን መጠቀም ይችላሉ፡፡

ይሁን እንጅ ወረዳው ወይም ከተማ አስተዳደሩ ለሚያከናውኑአቸው ስራዎች የክልሉ መንግስት ለዋጋ ንረት ማስተካከያ ተጨማሪ በጀት የማይመድብ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

9.3. ሙሉ በሙሉ በረጂ ድርጅቶችና በሌሎች መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅትቶች በጀት ተመድቦላቸው የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ፋይናንስ የሚያደርጉ ድርጅቶች ፈቃደኛ ከሆኑና የግዥ ስርዓታቸው የሚፈቅድ ከሆነ ይህን የዋጋ ንረት ማስተካከያ ቀመር መጠቀምና መፈፀም ይችላሉ፡፡

Remove Watermark Wondershare PDFelement

9.4. በመቀናጀ የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ፡- መንግስት የራሱን ድርሻ አስልቶ በጀት የሚመድብ ሆኖ ቀሪውን መቀናጀ ፋይናንስ የሚያደርጉ አካላት እንዲያዉቁትና ፈቃደኛ ከሆኑና የግዥ ስርዓታቸው የሚፈቅድ ከሆነ ይህን የዋጋ ንረት ማስተካከያ ቀመር መጠቀም ይቻላል። ይህንም እያንዳንዱ መ/ቤት ኃላፊነት ወስዶ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ ይኖርበታል።

9.5. የዋጋ ንረት ማስተካከያ አከፋፈሉ ወጥ በሆነ መንገድ የሚፈፀም ሆኖ ይህ የተመደበው ገንዘብ ከክልሉ የካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በጀት በላይ ሆኖ ከተገኘ እያንዳንዱ መ/ቤት ፕሮጀክቶችን ገምግሞ እና ወጥ የሆነ መስፈርት አውጥቶ በመስፈርቱ መሰረት ቅደም ተከተል አዉጥቶ ተግባራዊ እንዲያደርግ የተወሰነ በመሆኑ በአፈጻጸም ላይ ልዩ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል።

10. የክልል ቢሮዎች ወይም ተቋማት በዋጋ ንረት ማሻሻያ የሚደረግባቸው ፕሮጀክቶችን በጥንቃቄ በመገምገምና በመለየት ከመጋቢት 30/2014 ዓ.ም በፊት የውል ስምምነት የተገባባቸው፤ የፕሮጀክቶችን አፈጻጸምና ለቀሪ ስራዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ መጠን በጥንቃቄ ተሰልቶ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተረጋግጦ ለገንዘብ ቢሮ የዋጋ ንረት ማሻሻያዉን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

11. በክልላችን የሁሉን አቀፍ ገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም /URRAP/ የሚሰሩ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ይህ የዋጋ ንረት ማስተካከያ አይመለከታቸውም።

12. ከዚህ በፊት የወጡ የዋጋ ንረት ማስተካከያዎች የተሻሩና በዚህ የዋጋ ንረት ማስተካከያ የተተኩ መሆኑ ታውቆ በዚህ አግባብ ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል።

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

ገንዘብ ቢሮ- ባህር ዳር

ሰኔ 2014 ዓ.ም